# አብዮታዊት ኢትዮጵያ

12

★ በትጥቅ መብቃት

★ የወዝ አደሩ የሙያ ማኅበር አብዮታዊ ሚና

★ ወዝ አደሩ ይናገር

★ ዘር ቀለም ? ወይስ መደብ ? ?

ጥቅምት ፲፩—፲፱፻፸፱ ዓ. ም.

## ርእሰ አንቀጽ ።

# በትጥቅ መብቃት

አብዮታችን በየካቲት ወር ፲፱፻፷፮ ዓ. ም. ተቀጣጥሎ ያለማቋረጥ እየገፋ አሁን ከሚገኝበት ከፍተኛ ደረጃ ደርሷል ። በገሀድ በአዋጅ የተገኙት ድሎች እጅግ ብዙና ከፍተኛ ናቸው ። ነገር ግን የኢትዮጵያን አብዮት አጠቃላይ ሂደት በምንመለከትበት ጊዜ ከነዚህ ድሎች ጋር አያይዘን ሐቀኛ ወዳጅን ከጠላት በመለየት በኩል ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ያገኛቸውን ድሎች መመልከት አለብን ።

ተደጋግሞ እንደተነገረው ከየካቲት ወዲህ ብዙ ኃይሎች ከአብዮቱ ባቡር እየወረዱ ወደ ፀረ አብዮት ሠፈር ተደባልቀዋል ። አንዳንዶች ደግሞ ፀረ አብዮት ሠፈርም ተደባልቀው እየታገሉ ለተወሰነ ጊዜ ተራማጅ መስለው ማወናበድ ችለው ነበር ። በእንደዚህ ዓይነቱ አደገኛ ሁኔታ በሰፊው ሕዝብ መሀከል ተራማጅ መስለው የተሰገሰጉ አድኃሪዎች በአብዮቱ ሠፈር የርእዮተ ዓለም ውዥንብር በመንዛት ፤ ወዳጅና ጠላት በቅጡ እንዳይለይ በማከላከል የአብዮቱን ዕድሜ ለማሳጠር ከፍተኛ ጥረት ሲያደርጉ ቆይተዋል ።

የሰፊውን ሕዝብ ትግል ለማደናቀፍ ወዳጅ መስለው የተደባለቁ ኃይሎችን ለማጋለጥና ለሕዝቡ ሠፈር ጥንካሬ ለመስጠት እጅግ መራራ የሆነና የማያወላውል ትግል ተደርጓል ። ዛሬ አርሶ አደሩ ወዝአደሩ ፤ ወጣቱ ፤ ጭቁን ሴት ፤ ተራማጁ መለዮ ለባሹና ምሁራን « ለነቃ ለተደራጀና ለታጠቀ ሕዝብ ትግል » ተሰልፈዋል ። በሰፊው ሕዝብ ሠፈር የዛሬ ዓመት የነበረው የርእዮተ ዓለም ውዥንብር ወድሟል ። የኢትዮጵያ ሀቀኛ ተራማጆች በሙሉ ኃይላቸውን አስተባብረው ባካሔዱት መራራ የርእዮተ ዓለም ትግል እንደነ ኢህአፓ ያሉት የቀኝ ክንፍ ንዑስ ከበርቴ ቡድኖች ከነቀልባሽ መፈክሮቻቸውና መሳፍንታዊ አቋሞቻቸው ተጋልጠው ከታሪክ ትቢያ መጣያ ውስጥ በመውደቅ ላይ ናቸው ። ሁለት ዓመት ሙሉ የአብዮቱን ሂደት በማደናቀፍ ይህ ነው የማይባል ውዥንብር ፤ ሴራና ተንኮል ሲነዙ ከቆዩ በኋላ ከመሳፍንቱ ፤ ከነሲ አይኤና ከጠቅላላው ቀልባሽ ኃይሎች ጋር ባላቸው የአቋም ፤ የድርጅትና የትጥቅ ትብብር ተጋልጠው እነሆ ርቃናቸውን ቆመዋል ።

በዚህ በኩል በተደረገው ከፍተኛ የፖለቲካ ተጋድሎ የተነሣ በአሁኑ ጊዜ የተለያዩ ኃይሎች ይዘው የሚታገሉበት አቋም በምንም ሰበብና አስባብ ተሸፋፍኖ ሊድበሰበስ የማይችልበት ሁኔታ ላይ ተደርሷል ። በአሁኑ ጊዜ ሁለት ግንባሮች ተፋጠዋል ።

የነኢህአፓ ግንባር ጠቅላላውን አድኃሪ ኃይሎችን አስተባብሮ እስካሁን የተገኙትን ድሎች በሙሉ ለመቀበልስ የሚታገል ግንባር ነው ። ይህ ዛሬ በአንዳንድ ተራማጆች ዘንድ የማይመስል የማጥላላት « አንድ ቡድን ሆን ብሎ ስም ለማጥፋት የሚነዛው » ፕሮፓጋንዳ ሊመስል ይችላል። ይህንን የሚያስቡ « ተራማጆች » ከጥቂት ወራት በፊት ኢህአፓ የተባለው ድርጅት አብዮታዊነት አክትሟል ። ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት የሚባለው መፈክር የቀልባሾች መፈክር ነው ፤ በቅርብ ጊዜ ውስጥ በኢትዮጵያ ከፍተኛ የኃይሎች መሸጋሸግ ይመጣና ኢህአፓ በፀረ አብዮቱ ሠፈር ይቆማል ፤ ኢህአፓ በፖለቲካ ትግሉ እየተጋለጠ ሲሔድ ወደ « ማጅራት መችነት ድርጅት » ይለወጣል እየተባለ ሲጻፍና ሲነገር ማመን ያቃታቸው ወላዋዮች ነበሩ ። ነገር ግን መጭው ጊዜ ቁልጭ አድርጎ እንደሚያሳየን ከዛሬ ይልቅ የዛሬ ወር ፤ ከዛሬ ወር ይልቅ የዛሬ ስድስት ወር የቀኙ ክንፍ ንዑስ ከበርቴ ቡድን ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት በምትለው የቀልባሾች መፈክሩ ላይ በመሬት ጉዳይና በሌሎችም አብዮት ነክ ጉዳዮች ላይ ከመሳፍንቱና ከነሲአይኤ የሚያስተባብረው አቋም ወስዶ ይበልጥ እንደሚጋለጥ ቅንጣት አንጠራጠርም ።



በዚህ የቀልባሾች ግንባር መፈጠር የተነሣ የሰፊው ሕዝብ ወገኖች ኃላፊነት ሲወድቅባቸው እናያለን ። እነሱም በበኩላቸው ጥቃቅን ልዩነቶቻቸውን አቻችለው ኃይላቸውን ማስተባበርና የፀረ አብዮት ኃይሎችን ግፊት መቋቋም አለባቸው ።

በሌላ በኩል ደግሞ ተራማጆች ፈጽሞ መርሳት የሌለባቸው ጉዳይ አለ ። ዘለዓለማቸውን የፖለቲካ ድል ፤ ዘለዓለማቸውን የርእዮተ ዓለም ድል እየተጐናጸፉ መቀጠል አይችሉም ። በትጥቅም በኩል ብቁና ዝግጁ መሆን አለባቸው ። በዚህ በኩል አንድ ግልጥ የሆነ ጉዳይ አለ ። በአድኃሪነታቸው ሙሉ ተጋልጠው ተራማጅ መስለው ለማወናበድ የማይችሉ ኃይሎች በሕዝቡ ላይ መሣሪያ ይዘው ለማመጽ የሚቀድማቸው የለም ። ነገር ግን በሕዝብ ላይ መሣሪያ የሚያነሡ እነሱ ብቻ አይደሉም ። አብዮቱ እየገፋ ሲሔድ ሌሎች ኃይሎች ከሕዝቡ ጋር ተጻራሪ የሆነ ቅራኔ ውስጥ ይገባሉ ። መከራከር የማይቻልበት ፤ ተራማጅ መስሎ ማወናበድ የማይቻልበት ሁኔታ ይፈጠራል ። ማርክስ እንዳለው በእንዲህ ዓይነቱ ጊዜ መከራከር እንደመሣሪያ መቆጠሩ ይቀርና የማይቀረው የመሣሪያ ክርክር ይጀመራል ።

ስለሆነም ዛሬ የቀኙን ክንፍ ንዑስ ከበርቴ ቡድን ፀረ አብዮት ኃይሎች ያስታጠቁትን መሣሪያ ይዞ በአብዮቱ ላይ እንዲያምፅ የገፋፋው ፤ ሀቀኛ ተራማጆች በርእዮተ ዓለሙ ትግል የተጐናጸፍነው ድል ነው ። ጥያቄው እንግዲህ አጭር ነው ። በረዥም ጊዜ መራራ ትግል የተገኘው የርእዮተ ዓለም ድል በሰፊው ሕዝብ ሠፈር የሰፈነው የአሰላለፍ ጥራት መድረሻ ባጡ አድኃሪዎች ትጥቅ ይመታ ወይንስ ተራማጆች የፖለቲካ ድላቸውን በትጥቅ ተከላክለው እንዲያብቡና እንዲለመልም ያድርጉት ?

የኢትዮጵያ ተራማጆች በመሠረቱ የሰፊው ሕዝብ ድል የሚገኘው በነቃ ፤ በተደራጀና በታጠቀ ሕዝብ ትግል እንደሆነ ያውቃሉ ። ሐቀኛ ተራማጆች እስካሁን ያካሄዱት ትግል ይህንን የአብዮት ፋና ለማድበስበስና የሕዝቡን ትግል የማያዋጣ አቅጣጫ ለማስያዝ ከሚፍጨረጨሩ አድኃሪያን አድርባዮችና ወላዋዮች ጋር ነው ። ስለሆነም ይህ ትክክለኛ መሥመራቸው ድልን ፤ ተቀዳጅቶ ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከየአቅጣጫው ንቃት ፤ ድርጅት ፤ ትጥቅ እያለ የቆየ ጥሪያቸውን ጨብጦ በሚያስተጋባበት ባሁኑ ወቅት ተራማጆች ላገኙት የፖለቲካ ድል ድርጅታዊና ትጥቃዊ ብቃትን ችላ ይላሉ ብሎ ማሰብ የአድኃሪዎችን ደደብነት ይጠይቃል ።

የኢትዮጵያ ተራማጆች የተጐናጸፏቸውን ድሎች ላለማስደፈር ፤ የአብዮቱን መቀልበስ ሳይሆን ወደፊት መግፋት ለማረጋገጥ በአሁኑ ጊዜ የሰፊው ሕዝብ መታጠቅ አንገብጋቢ ጥያቄ ነው ብለው ያምናሉ ። ስለሆነም በዚህ የአብዮታችንን መግፋት ወይም መቀልበስ የሚመለከት ዐቢይ ጥያቄ ላይ እያንዳንዱ ቡድንም ሆነ ግለሰብ የሚወስደው አቋም ከመደቦች ትግል ተለይቶ የሚታይበት ቅንጣት ነገር የለውም ። በአሁኑ ጊዜ አብዮቱን ለመቀልበስ ያሰፈሰፉት ኃይሎች ታጥቀዋል ። አብዮቱን ለመከላከል የሚፈልጉ ኃይሎችም የግድ መታጠቅ አለባቸው ። ነገሩ ከፀሐይ በደራ ሁኔታ ግልጥ ሆኖ መታየት አለበት አብዮታችንን ፤ ነፃነታችንን ክብራችንን የሚሉ ታጋይ ኢትዮጵያውያን ከምንም አድርባይነት ፤ ከምንም የቡድን ስሜት በላይ በማሰብ ሰፊው ሕዝብ ዛሬ ነገ ሳይል እንዲታጠቅ ይታገላሉ ። ቅልበሳን ፤ ውርደትን ፤ ባርነትን በጭቁን የኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ መልሰን እንጭናለን የሚል ቅዠት የተቆራኛቸው ፀረ ሕዝቦች ትጥቅን ይቃወማሉ ። በዛሬው ወቅት በሀገራችን ከፀረ አብዮቱም ሠፈር ከአብዮቱም ሠፈር ሳይሆኑ መሐል ሆኖ መቆየት እንደማይቻል ሁሉ የትጥቅን ጥያቄ በመደገፍና ባለመደገፍ መሐከል ለመዋለል የሚቻልበት ወቅት አክትሟል ።

ሰፊው ሕዝብ ይታጠቅ ፤
አብዮታዊት ኢትዮጵያ ።